## ተራዳኝ ሚካኤል

ተራዳኝ ሚካኤል ከእግር ወድቄ አለሁ

አማልደኝ ከንጉሥ እለምንሃለሁ

በጠራችህ ጊዜ ቅድስት አፎምያ

ሰይጣን ሲፈትናት ከልቅሶ ብካያ/ለቅሶ/

እንደደረስክላት ለእኔም ድረስልኝ

የሚፈትነኝን ጠላቴን ጣልልኝ

አዝ . . . . . .

ርግብ አዕይንት ልብስህ የመብረቅ

ከእሳት አድነን እንዳልዘፈቅ

ለኀዘን ጭንቀቴ ፈጥኖ የሚደርስ

ሚካኤል ነው ለእኔ ልቤን የሚያድስ

አዝ . . . . . .

ተልኮ ይመጣል ከድንግል ማርያም

ጠዋትና ማታ ምን ጊዜም በሠርክ

ሚካኤል ፈጣን ነው የሰላም መልአክ

አዝ . . . . . .

የምትመግባቸው ለእስራኤል መና

ሚካኤል እፁብ አለህ ልዕልና

የምትፋጠን ነህ ምን ጊዜም ለሣህል

ምሕረት አውርድልን ቅዱስ ሚካኤል